የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ

# ADDIS NEGARI GAZETA

OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA

---------ዓመት ቁጥር ፸፭/፪ሺ፲ ፬
አዲስ አበባ ________ሐምሌ ፲ ቀን ፪ሺ፲ ፬

በአዲስ አበባ ከተማ
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

--------- YEAR NO.75/2022
ADDIS ABABA 17th July, 2022

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፸፭/፪ሺ፲፬
የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሥነ-ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ
ገጽ………………

CONTENTS

Proclamation Number 75/2022
Addis Ababa City Government Ethics and Anti-Corruption Commission Establishment Proclamation

Page

## አዋጅ ቁጥር ፸፭/፪ሺ፲፬

## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሥነ-ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ

የከተማው አስተዳደር ሙስና እና ብልሹ አሰራር የከተማዋን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ እድገት የሚጎዳ ተግባር መሆኑን በመገንዘብ፤

ከተማዋ የተያያዘችውን የእድገት ጉዳና እና የዲሞክራሲ ስርዓት ግንባታ እንዲፋጠንና ቀጣይነት ያለው እንዲሆን ሙስናን እና ብልሹ አሰራርን መከላከል አስፈላጊ በመሆኑ፣

## Proclamation Number 75/2022

## Addis Ababa City Government Ethics and Anti-Corruption Commission Establishment Proclamation

**WHEREAS,** the city government has recognized that corruption and mal-administration is detrimental to the social, economic, and political development of the city;

**WHEREAS,** it has been found necessary to prevent corruption and mal-administration to accelerate the development endeavors and democratization system building of the city and to ensure the sustainability of the thereof;

ለዚህም ሙስና እና ብልሹ አሰራርን የማይሸከም እና ይህንኑ በብቃት ለመዋጋት ዝግጁ የሆነ የከተማው ነዋሪን መፍጠር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በከተማው አስተዳደር ሙስና እና ብልሹ አሰራርን በብቃት መዋጋት የሚችል ተቋማዊ እና የአሰራር ነጻነት ያለው ተቋም ማቋቋም አስፈላጊ በመሆኑ፤

የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት በፌዴራል የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅን ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፴፮/፪ሺ፲፫ አንቀጽ ፫ ንዑስ አንቀጽ (፫) እና በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፩ሺ፱፻፺፭ (እንደተሻሻለ) አንቀጽ ፳፱ እናአንቀጽ ፲፬ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተራ ፊደል (ሀ) መሠረት ይህን አዋጅ አውጥቷል፡፡

WHEREAS, as a result of this, it has been found necessary to have a city resident that renounce corruption and mal-administration and effectively fight the thereof;

WHEREAS, it has been found necessary to establish an institution that effectively fight corruption and mal-administration in the city government and has an operational independence;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Sub-Article (3) of Article 3 of the revised Proclamation for the Establishment of the Federal Ethics and Anti-Corruption Commission Proclamation Number 1236/2021 and Article 29 and letter (A) of Sub-Article (1) of Article 14 of the Revised Addis Ababa City Government Charter Proclamation Number 361/2003 (as amended), the Addis Ababa City Council has issued this Proclamation.

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሥነ-ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፸፭/፪ሺ፲፬" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## PART ONE
## GENERAL PROVISIONS

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as: "The Addis Ababa City Government Ethics and Anti-Corruption Commission Establishment Proclamation Number 75/2022."

**፪. <u>ትርጓሜ</u>**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩. **"ከተማ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፤

፪. **"አስተዳደር"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤

፫. **"ምክር ቤት"** ማለት የከተማው ምክር ቤት ነው፤

፬. **"ኮሚሽን"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሥነ-ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን ነው፤

፭. **"ኮሚሽነር ወይም ምክትል ኮሚሽነር"** ማለት እንደቅድመ ተከተሉ ኮሚሽኑን በበላይነት የሚመራ የኮሚሽኑ ኮሚሽነር ወይም ምክትል ኮሚሽነር ነው፤

፮. **"የመንግሥት መሥሪያ ቤት"** ማለት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በአስተዳደሩ በጀት የሚተዳደርና የከተማ አስተዳደሩ ሥራዎች የሚከናወኑበት ማናቸውም መስሪያ ቤት ነው፣

**2. <u>Definition</u>**

In this Proclamation, unless the context requires otherwise:

1. **"City"** means the Addis Ababa city;
2. **"Government"** means the Addis Ababa City Government;
3. **"Council"** means the Council of the city;
4. **"Commission"** means the Addis Ababa City Government Ethics and Anti-Corruption Commission;
5. **"Commissioner or Deputy Commissioner"** means a commissioner or deputy commissioner that superiorly leads the commission respectively;
6. **"Public Office"** means any office that is fully or partially run its activities by the budget of the city government and where the activities of the city administration are carried out;

፯. **"የመንግሥት የልማት ድርጅት"** ማለት የአስተዳደሩ የባለቤትነት ድርሻ በሙሉ ወይም በከፊል ያለበት የአስተዳደሩ የልማት ድርጅት ወይም የአክሲዮን ማኅበር ነው፤

፰. **"ህዝባዊ ድርጅት"** ማለት በማንኛውም አግባብ ከአባላት ወይም ከሕዝብ የተሰበሰበ ወይም ለህዝባዊ አገልግሎት ታስቦ የተሰበሰበ ገንዘብ፣ ንብረት ወይም ሌላ ሀብትን የሚያስተዳድር አካልንና አግባብነት ያለው ኩባንያን የሚያካትት የግል ዘርፍ ሲሆን የሚከተሉትን አያካትትም፡-

ሀ) የሀይማት ድርጅት

ለ) የፖለቲካ ድርጅት (ፓርቲን)

ሐ) የዓለም አቀፍ ድርጅትን፣ እና

መ) ዕድርና ተመሳሳይ ባህላዊ ወይም ሃይማኖታዊ ይዘት ያለው ማህበርን፤

፱. **"ባለሥልጣን"** ማለት በየደረጃው ያለ የከተማው አስተዳደር የምክር ቤት አመራር ወይም አባል ወይም በአስተዳደሩ መሥሪያ ቤት ወይም በልማት ድርጅት ወይም በህዝባዊ ድርጅት ውስጥ በኃላፊነት እንዲያገለግል በህዝብ የተመረጠ ወይም የተሾመ ወይም የተመደበ ሰው ሲሆን የስራ አመራር ቦርድ አባልን ይጨምራል፤

7. **"Public Enterprise"** means a public enterprise or share company where the city government has a full or partial ownership;

8. **"Public Organizations"** means an organ that manages money, property, or other resources that are collected in any way from members or the public or for providing public services, and includes the relevant companies from the private sector; however, it shall not include the following:
   A. Religious institutions;
   B. Political organizations (parties);
   C. International organizations; and
   D. *'Idir'* and other similar cultural and religious associations;

9. **"Public Official"** means a person who is elected as a leader or member of the council of the city government at all levels or appointed to serve as an official in public offices or enterprises of the city; and it includes members of a board;

፲. **"የመንግስት ሠራተኛ"** ማለት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 8 ውስጥ ከተጠቀሱት ውጭ ያለና በከተማ አስተዳደሩ በመንግስት ሠራተኞች አዋጅ መሠረት በቋሚነት ወይም በጊዚያዊነት ተቀጥሮ ወይም ተመድቦ የሚሠራ ሰው ነው፣

፲፩. **"የመንግሥት የልማት ድርጅት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ"** ማለት በአስተዳደሩ የልማት ድርጅት ወይም በህዝባዊ ድርጅት ውስጥ በቋሚነት ወይም በጊዜያዊነት የሚሠራ ሰው ነው፣

፲፪. **"ስነ ምግባር ትምህርት"** ማለት በአንድ ሕብረተሰብ የጋራ ሕይወት የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ውስጥ መንግሥት በሚሰጠው አገልግሎትም ሆነ በግሉ ዘርፍ ውስጥ ተቀባይነት ያለውንና የሌለውን ጥሩና መጥፎውን ለመለየት፣ ለመግለጽና ሥርዓት ለማስያዝ እንዲሁም የሙያና የግብረገብ ግዴታችንን ለመወጣት የሚያስችል ሕግና ደንብ ወይም ደረጃ ሲሆን መጥፎውን በመተው መልካሙን ነገር እንድንከተል፣ ለሙስናና ብልሹ አሰራር እንዳይጋለጥ ለማድረግ፣ የህዝብ አግልጋይነት ባህል እንዲዳብር የሚመራ ወይም የሚያስተምር ነው፡፡

10. **"Public Employee"** means any person who is, other than those referred to under Sub-Article 8 of this Article, permanently of temporarily employed or assigned in public offices of the city administration as per the civil servants' Proclamation of the city government;

11. **"Employee of a Public Enterprise or Public Organization"** means a person that is working in the public enterprises or public organizations of the city government either permanently or temporarily;

12. **"Ethical education"** means a law or standard that helps or teaches us to follow the right path, protect us from corruption and mal-practices, and develop a culture of serving the public as well as to identify, describe, and regulate issues that are acceptable or not in government services or in the private sector in the routine activities of a society or carry out one's professional or moral obligation;

፲፫. **“የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል”** ማለት በመንግሥት መስሪያ ቤት ወይም በመንግሥት ልማት ድርጅት ወይም በህዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ ኮሚሽኑ ስራውን በየተቋማቱ ለማሰራት የሚያደራጀው አደረጃጀት ነው፤

፲፬. **“ጠቋሚ”** ማለት ሊፈጸም ነው ብሎ ያመነውን ወይም የተፈጸመ የሙስና ወንጀል ወይም የሀብት ምዝገባ ትክክለኛ አለመሆኑን የሚመለከት መረጃ ለኮሚሽኑ ወይም ለሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎች የሚያቀርብ ማንኛውም ሰው ነው፤

፲፭. **“ሰው”** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

## ፫. <u>የጾታ አገላለጽ</u>

በዚህ አዋጅ ውስጥ በወንድ ፆታ የተደነገገው የሴትንም ጾታ ያካትታል፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>ስለኮሚሽኑ መቋቋም፣ ሥልጣንና ተግባር</u>

## ፬. <u>የኮሚሽኑ መቋቋም</u>

፩. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን (ከዚህ በኋላ **"ኮሚሽን"** እየተባለ የሚጠራ) የከተማው አስተዳደር መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

፪. የኮሚሽኑ ተጠሪነት ለከተማው ምክር ቤት ነው፡፡

13. **“Ethics Liaison Units”** means an organization that is organized by the commission in public offices or public enterprises so as to operate its activities;
14. **“Whistleblower”** means any person that reports an intended corruption activity or committed one or any information concerning an inaccurate asset registration to the commission or ethics liaison units;
15. **“Person”** means any natural or juridical person.

## 3. <u>Gender Expression</u>

In this Proclamation, any expression in the masculine gender shall include the feminine.

## <u>PART TWO</u>

## <u>ABOUT THE ESTABLISHMENT, POWER AND DUTIES OF THE COMMISSION</u>

## 4. <u>Establishment of the Commission</u>

1. The Addis Ababa City Government Ethics and Anti-Corruption Commission (hereinafter referred to as the **“Commission”**) is hereby established as a public office of the city government by this Proclamation;
2. The commission shall be accountable to the Council of the city.

**፭. የኮሚሽኑ አቋም**

ኮሚሽኑ፡-

፩. በከተማው ከንቲባ አቅራቢነት በምክር ቤት የሚሾም ኮሚሽነር እና ምክትል ኮሚሽነሮች፤

፪. ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ የሥራ ክፍሎችና ሠራተኞች፣

ይኖሩታል፡፡

**፮. ስለ ኮሚሽኑ የአሠራር ነፃነት**

ኮሚሽኑ ሙስናንና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል በሚያከናውነው ተግባር ከማንኛውም ሰው ወይም አካል ጣልቃ ገብነት ነፃ ነው፡፡

**፯. የኮሚሽኑ ዓላማዎች**

ኮሚሽኑ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

፩. የሥነ-ምግባርና የፀረ ሙስና ትምህርቶችን በማስፋፋት የሞራል እሴቶችን በመገንባት የነቃ እና ሙስናን ሊሸከም የማይችል ኅብረተሰብ መፍጠር፤

፪. የሙስና ወንጀልን እና ብልሹ አሠራርን መከላከል፤

፫. ነዋሪው የፀረ-ሙስና ትግል ባለቤት እንዲሆን ማድረግ፤

**5. Organization of the Commission**

The Commission shall have:

1. a commissioner and deputy commissioners who will be appointed by the Council through the nomination of the Mayor of the city;
2. The necessary departments and employees for the work.

**6. Institutional Independence of the Commission**

The commission shall be free from any interference from any individual or any organ in its efforts to prevent corruption and mal-administration.

**7. Objectives of the Commission**

The commission shall have the following objectives:

1. Create a vibrant society that renounce corruption through promoting ethical and anti-corruption education and building moral values;
2. Prevent corruption crimes and mal-administration;
3. Make sure that the residents of the city take responsibility in the fight against corruption;

፬. በጸረ ሙስና ትግል ብልሹ አሰራርን ለማስቀረት ግልጽና ተጠያቂነት ያለው አሰራር ሥረዓት ማስፈን፤

፭. በህግ የተሰጡትን ስልጣንና ተግባር ለመፈጸም የሚያስችል ተቋማዊ አቅም መገንባት፡፡

**፰.**<u>**የኮሚሽኑ ሥልጣንና ተግባር**</u>

ኮሚሽኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣

፩. ሀገራዊ የፀረ-ሙስና ፓሊሲ እና ስትራቴጂ መሠረት በማድረግ ከተማ አቀፍ ፖሊሲና ስትራቴጂ ያዘጋጃል፣ ለምክር ቤት ያቀርባል፤ ሲጸድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

፪. በከተማው አስተዳደር መሥሪያ ቤቶች፣ የልማት ድርጅቶች እና በህዝባዊ ድርጅቶች የሚሾሙ ወይም የሚመደቡ ወይም የሚቀጠሩ የሥራ ኃላፊዎች እና ሠራተኞች ሥራ ከመጀመራቸው በፊት የሥነ-ምግባር እና የሙስና መከላከል ሥልጠና እንዲወስዱ ያደርጋል፤

4. Establish a transparent and accountable procedural system to prevent mal-administration in the effort of fighting against corruption;
5. Build an institutional capacity that enables it to undertake the power and duties given to it under the law.

**8. <u>Power and Duties of the Commission</u>**

The commission shall have the following power and duties:

1. Prepare city-wide policy and strategy based on the national anti-corruption policy and strategy; submit same to the council; implement the thereof upon approval; follow up the implementation of same;
2. Cause the provision of ethical and corruption prevention trainings to various officials and employees that are appointed or assigned or hired in the public offices, public enterprises, and public organizations of the city government before commencing their work;

፫. በአስተዳደሩ መሥሪያ ቤቶች ፣ በልማት ድርጅቶች እና በህዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ ለሙስናና ብልሹ አሠራር የተጋለጡ እና ሊጋለጡ የሚችሉ የአሠራር ሥርዓቶችን በማጥናት ወይም እንዲጠኑ በማድረግ የተሰጡ የመፍትሔ ወይም የማሻሻያ ሃሣቦችን ያቀርባል፣ ተግባራዊ መሆናቸውን ይከታተላል፣ በማይፈፅሙት ላይ ተገቢ የሆኑ እርምጃ እንዲወሰድ በሕግ የመመርመርና የመክሰስ ሥልጣን ላለው አካል ያቀርባል፤

፬.ኮሚሽኑ ሙስና ለመፈፀም የሚያስችል ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን ሲጠረጥር ወይም ጥቆማ ሲደርሰው ድርጊቱ ከመፈፀሙ በፊት አስቸኳይ የሙስና መከላከል ሥራ በመሥራት ሂደቱ እንዲቋረጥ ወይም አስፈላጊውን ማስተካከያ ያደርጋል፤ በተደረገው ክትትል ሙስና ስለመፈፀሙ ወይም ሊፈጸም እንደሚችል ጥርጣሬ ሲኖረው በሕግ የመመርመርና የመክሰስ ሥልጣን ላለው አካል ያቀርባል፤

3. Study or cause the study of working procedures that are susceptible to corruption or potential ones in the public offices, public enterprises, and public organizations of the city government and present the recommended solution or adjustments; follow up the execution of the thereof; report to an organ that has the power to investigate and prosecute those who fails to implement the thereof in order to take the proper measures;

4. When the commission suspects or has got a report on the preparation progress of a corruption activity, it shall carry out a rapid corruption prevention work and terminate the process or take the necessary adjustments; when the commission has a suspicion that corruption has been made or is likely to take place during the process, it shall report same to an organ that has the power to investigate and prosecute;

፭. የከተማው ነዋሪ ሕዝብ ተመራጮች፣ የአስተዳደሩ ተሿሚዎች፣ የአስተዳደር ሠራተኞች፣ የአስተዳደሩ የልማት ድርጅቶች እና የሕዝባዊ ድርጅት የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች ሀብታቸወን እንዲያሳውቁ፣ እንዲያስመዘግቡ፣ ትክክለኛነቱ እንዲረጋገጥ ያደርጋል፤ መረጃውን በአግባቡ አደራጅቶ ይይዛል፤ ለሕዝብ ተደራሽ እንዲሆን ያደርጋል፤

፮. የሀብት ምዝገባ ትክክለኛነትን ለማረጋገጥ እና ተደራሽ ለማድረግ የሚያስችል ሶፍት ዌር ያበለጽጋል፣ ጥቅም ላይ ያውላል፣ ያስተዳድራል፣ አግባብነት ያላቸው አካላት መረጃ ሲጠይቁ ይህንኑ ከዳታ ቤዝ የተገኘውን መረጃ ይሰጣል፤

፯. የከተማው ነዋሪ ሕዝብ ተመራጮች፣ የአስተዳደሩ ተሿሚዎች፣ የአስተዳደሩ ሠራተኞች፣ የአስተዳደሩ የልማት ድርጅቶች እና የህዝባዊ ድርጅት የሥራ ኃላፊዎች እና ሠራተኞች ከተሰጣቸው ኃላፊነት፣ ከመቆጣጠር እና ከመወሰን ሥልጣን ጋር በተያያዘ የሚፈጠር የጥቅም ግጭትን ለመከላከል የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ተገቢ የሆነ እርምጃ እንዲወሰድ በሕግ የመመርመርና የመክሰስ ሥልጣን ላለው አካል ያቀርባል፡፡ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፤

5. Ensure the declaration and registration of the assets and financial interests of the elected public officials of the city residents, appointees and employees of the city government, officials and employees of the public enterprises and public organizations of the city government; cause the verification of the thereof; organize and keep the information properly; make it accessible;

6. Develop, use, and manage a software that enables to verify the authenticity of the declaration and registration of assets and makes it accessible; provide the information obtained from the database to the relevant organ upon the request of the thereof;

7. Establish a system that enables to prevent the conflict of interest of elected public officials of the city residents, appointees and employees of the city government, officials and employees of the public enterprises and public organizations of the city government that would be created in connection with their mandate, authoritative power and decision making; report same, if it has been necessary, to an organ that has the power to investigate and prosecute the thereof for taking an appropriate measure; the details shall be specified through a Regulation;

፰. ሙስናን በመታገል እና በመከላከል ረገድ ጥሩ ውጤት ያስገኙ መሥሪያ ቤቶችን፣ ድርጅቶችን፣ ግለሰቦችን፣ እና ክበባትን አወዳድሮ እውቅና የሚያገኙበትን እና ለሽልማት የሚበቁበትን ሥርዓትና መለኪያ ይዘረጋል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፤ዝርዝር አፈጻጸሙ በመመሪያ ይወሰናል፤

፱. ለከተማው ነዋሪ ሕዝብ ተመራጮች፣ ለአስተዳደሩ ተሿሚዎች፣ ለአስተዳደሩ ሠራተኞች፣ ለአስተዳደሩና ለህዝባዊ ደርጅት የሥራ ኃላፊዎች እና ሠራተኞች የሚያገለግል የሥነ-ምግባር ደንብ ያዘጋጃል ወይም እንዲዘጋጅ ያደርጋል፣ ሲጸድቅ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

፲. በአስተዳደሩ መሥሪያ ቤቶች፣ የልማት ድርጅቶች እና ህዝባዊ ድጅቶች ውስጥ የሙስና እና ብልሹ አሠራር ተጋላጭነትን ጥናት ያካሂዳል፣ እንደአስፈላጊነቱ ለነዋሪው ይፋ ያደርጋል፤

፲፩. የሥነ-ምግባር ግንባታ እና የሙስና መከላከል ተግባራትን ለመፈፀም የሚያስችሉ አደረጃጀቶችን በአስተዳደሩ መሥሪያ ቤቶች እና የልማት ድርጅቶች እንዲሁም በየደረጃው በሚገኙ የአስተዳደሩ የትምህርት ተቋማት ያደራጃል፤

8. Establish a system and criteria that enables to recognize and award offices, enterprises, individuals, and clubs, through competition, that register best performances in the fight against corruption and prevention of the thereof; implement same; the detail implementation shall be specified through directives;

9. Prepare or cause the preparation of a code of conduct for elected public officials of the city residents, appointees and employees of the city government; officials and employees of the public enterprises and public organizations of the city government; follow up the implementation of the thereof upon approval;

10. Conduct a study on corruption and mal-administration vulnerability in public offices, public enterprises, and public organizations of the city government; publicize same, as may be necessary;

11. Set up organizations that will carry out activities related to the promotion of ethics and prevention of corruption in public offices and public enterprises of the city government as well as in educational institutions of the city government at all levels;

፲፪. በከተማው አስተዳደር የፀረ-ሙስና ሕጎች መከበራቸውን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፣ ስለአፈፃፀማቸው የምክር አገልግሎት ይሰጣል፤

፲፫. በአስተዳደሩ መሥሪያ ቤቶች፣ የልማት ድርጅቶች እና ህዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ የሥነ-ምግባር መከታተያ ዳይሬክቶሬቶችን ወይም ቡድኖችን ወይም ባለሙያዎችን ከየተቋማቱ ጋር በመነጋገር ያደራጃል፣ ይመድባል፣ ያሰማራል፤

፲፬. በሀገሪቱ ሕግ እና ፓሊሲ መሠረት ዓለም አቀፍ እና አህጉራዊ የፀረ-ሙስና ኮንቬንሽኖችን እና ትብብሮች በከተማው ሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፣

፲፭. የሥነ-ምግባር ትምህርትን ለማስፋፋት እና መልካም ሥነ-ምግባርን ለመገንባት እንዲያስችለው የተለያዩ የኮሚኒኬሽንና ሚዲያ ዘዴዎችን ይጠቀማል፤

፲፮. የሙስና ወንጀል ምርመራ እና ክስ የመመሥረት ሥልጣን ከተሰጣቸው እና ከሌሎች አግባብነት ካላቸው አካላት የሥራ አፈፃፀም ሪፓርት ይቀበላል፤

12. Monitor and ensure the compliance of anti-corruption laws in the city government; provide consultation service on the implementation of the thereof;

13. Organize, assign, and deploy ethical liaison directorates, or teams, or experts in the public offices, public enterprises, and public organizations of the city government in consultation with same;

14. Cause the implementation of international and continental anti-corruption conventions and partnerships in the city pursuant to the laws and policies of the country;

15. Use various media outlets that helps to promote ethical education and enhance good ethics;

16. Receive performance reports from organs that have the power to investigate and prosecute corruption offences and other relevant organs;

፲፯. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በራሱ ስም ይከሳል፣ ይከሰሳል፤

፲፰. በሕግ የሚሰጡትን እና ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

**፱. <u>የኮሚሽነሩ ሥልጣንና ተግባር</u>**

፩. ኮሚሽነሩ የኮሚሽኑ የበላይ ኃላፊ በመሆን የኮሚሽኑን ሥራዎች ያደራጃል፣ ይመራል፣ ያስተዳድራል፣

፪. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ኮሚሽነሩ፡-

ሀ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፰ የተዘረዘሩትን የኮሚሽኑን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፣

ለ) የኮሚሽኑን መዋቅር፣ የደመወዝ ስኬል እና ጥቅማጥቅሞቻቸውን በማዘጋጀት ለምክር ቤት ያቀርባል፤ ሲጸድቅ ክፍያ ይፈፅማል፤ ዝርዝር አፈፃፀሙ በደንብ ይወስናል፣

ሐ) በዚህ አዋጅ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች እና የአስተዳደሩ የመንግሥት ሠራተኞች አዋጅ አጠቃላይ መርሆዎችን ጠብቆ ደንብ አዘጋጅቶ ለምክር ቤት ያቀርባል፣ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፣

17. Own property; enter into a contract; sue and be sued in its own name;
18. Carry out other activities that are given to it by the law and that helps it to attain its objectives.

**9. <u>Power and Duties of the Commissioner</u>**

1. The commissioner shall, being the head of the commission, organize, lead, and manage the activities of the commission;
2. Without prejudice to Sub-Article (1) of this Article, the commissioner shall:
   A. Execute the power and duties of the commission that are specified under Article 8 of this Proclamation;

   B. Preparethe structure of the commission, the salary and benefits of the employees of the commission and submit it to the council; effect payments upon approval; the detail implementation shall be specified through a Regulation;

   C. Prepare Regulations in conformity with the provisions specified under this Proclamation and the basic principles of the civil servants' Proclamation of the city government, and submit the thereof to the city council; implement same upon approval;

መ) ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞችን ይሾማል፣ ይመድባል፣ ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል፡፡ ዝርዝር አፈፃፀሙ በደንብ ይወሰናል፣

ሠ) የኮሚሽኑን ዓመታዊ የሥራ ፕሮግራም እና በጀት አዘጋጅቶ ለምክር ቤቱ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፣

ረ) ለኮሚሽኑ በተፈቀደለት በጀት እና በአዘጋጀው የሥራ ፕሮግራም መሠረት የአስተዳደሩን የፋይናንስ ሕግ ተከትሎ ገንዘብ ወጭ ያደርጋል፣

ሰ) ኮሚሽኑ ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደርጋቸው ግንኙነቶች ኮሚሽኑን ይወክላል፣

ሸ) የኮሚሽኑን ጠቅላላ የሥራ አፈፃፀምና የሂሣብ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለምክር ቤቱ ያቀርባል፣

ቀ) በሀብት ምዝገባ ትክክለኛነት ማረጋገጥ እና የጥቅም ግጭትን በማስተዳደር ሂደት አስፈላጊ በሆነ ጊዜ የማንኛውም ሰው ወይም ድርጅት የባንክ ሂሣብ እንዲፈተሽ እና አስፈላጊው መረጃ እንዲሰበሰብ ትዕዛዝ መስጠት ይችላል፣

D. Appoint, assign, hire, administer, and dismiss employees that are necessary for the work; the details of its implementation shall be specified through a Regulation;

E. Prepare the annual work program and budget of the commission, and submit it to the council; implement same upon approval;

F. Effect payments in accordance with the allocated budget and prepared work program of the commission as per the financials laws of the city government;

G. Represent the commission in its dealings with third parties;

H. Prepare the overall performance and financial reports of the commission, and submit it the council;

I. May give orders, if it is found necessary, for the examination and collection of the necessary information about the bank records of any individual or organization during the process of verifying the authenticity of an asset registration and managing a conflict of interest;

በ) በሀብት ምዝገባ ትክክለኛነት፣ በአስቸኳይ ሙስና መከላከል እና በሌሎች የሙስና መከላከል ተግባራት ለኮሚሽኑ ጥቆማ በመስጠታቸው ምክንያት የቂም በቀል እርምጃ ሊደርስባቸው የሚችሉ ጠቋሚዎች ሲኖሩ ተገቢውን ማጣራት በማድረግ በሕግ መሠረት ከለላ እና ጥበቃ እንዲደረግላቸው በሕግ ሥልጣን ለተሰጠው አካል ያስተላልፋል፣

ተ) ለኮሚሽኑ ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለኮሚሽኑ የሥራ ኃላፊዎች እና ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡

## ፲. የምክትል ኮሚሽነሮች ሥልጣንና ተግባር

፩. ምክትል ኮሚሽነሩ ተጠሪነቱ ለኮሚሽነሩ ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ) የኮሚሽነሩ ተግባሮች በማቀድ በማደራጀት፣ በመምራትና በማስተባበር ኮሚሽነሩን ይረዳል፣

ለ) በኮሚሽኑ መዋቅር መሠረት የስራ ክፍፍል በማድረግ ከኮሚሽኑ ዘርፎች ከፊሉን ይመራል፣

ሐ) ከኮሚሽነሩ ተለይተው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል፤

J. Inform the relevant organ which is entitled to provide protection for informants as per the law who are prone to vengeance as a result of reporting issues to the commission concerning the accuracy of asset registration, urgent prevention of corruption and other corruption prevention related activities;

K. May delegate part of his powers and duties to the officials and employees of the commission to the extent necessary for the effectiveness of the works of the commission.

## 10. Power and Duties of the Deputy Commissioners

1. The deputy commissioner shall, being accountable to the commissioner, have the following power and duties:
   A. Assist the commissioner in planning, organizing, managing, and coordinating the duties of the commissioner;
   B. Share activities of the commission according to its structure and run some departments of the thereof;
   C. Carry out other activities that are designated by the commissioner;

፪. ኮሚሽነሩ በማይኖርበት ጊዜ ኮሚሽነሩ የሚወክለው ምክትል ኮሚሽነር ኮሚሽነሩን ተክቶ ይሠራል፡፡

2. In the absence of the Commissioner, the Deputy Commissioner who is designated by the Commissioner shall act on behalf of the Commissioner.

**፲፩. <u>የኮሚሽነሩ እና የምክትል ኮሚሽነሩ የሥራ ዘመንና ከሥራ ስለመነሣት</u>**

፩. የኮሚሽነሩ እና የምክትል ኮሚሽነሩ የሥራ ዘመን ስድስት ዓመት ይሆናል፣ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ እንደገና ለአንድ የሥራ ዘመን ብቻ ሊሾም ይችላል፤

፪. ኮሚሽነሩ ወይም ምክትል ኮሚሽነሩ ከዚህ በታች በተመለከቱት ሁኔታዎች ካልሆነ በስተቀር የተሾሙበት የሥራ ዘመን ከማለቁ በፊት ከፈቃዱ ውጭ ከሥራው አይነሣም፡-

ሀ) አግባብነት ባለው የሥነ-ምግባር ደንብ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ተላልፎ ሲገኝ፣

ለ) ጉልህ የሆነ የሥራ ችሎታና የቅልጥፍና ጉድለት አሳይቷል ተብሎ ሲታመን፣

ሐ) በጤና ችግር ምክንያት ተግባሩን በተገቢው ሁኔታ ማከናወን የማይችል ሆኖ ሲገኝ፣

**11. <u>Term of Office and Removal from Office of the Commissioner and Deputy Commissioners</u>**

1. The term of office of the commissioner and deputy commissioners shall be six years; however, he may re-appointed for one term only if it is found necessary;
2. The commissioner or deputy commissioner may not be removed from his office, without his consent, before the end of his term of office except the following specified circumstances:
   A. When he has violated the specified provisions of the relevant code of conduct;
   B. When it is perceived that he has exhibited significant incompetence and inefficiency;
   C. When he is unable to carry out his duties due to health problems;

መ) ለጡረታ ዕድሜ ሲደርስ ይሆናል፣

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) በተራ ፊደል (ሀ) እና (ለ) ያሉት ድንጋጌዎች ተፈፃሚ የሚሆኑት በምክር ቤት ተጣርቶ ውሳኔው በአብላጫ ድምፅ ሲደገፍ ነው፡፡

**፲፪. ስለኮሚሽኑ ሠራተኞች ቅጥር ሁኔታ**

የኮሚሽኑ ሠራተኞች የቅጥር፣ አስተዳደርና ስንብት ሁኔታ በዚህ አዋጅ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች እና የከተማው አስተዳደሩ የመንግስት ሠራተኞች ሕግን እና መርሆዎችን መሠረት በማድረግ ምክር ቤቱ በሚያወጣው ደንብ መሠረት ይሆናል፡፡

**፲፫. ቃለ-መሃላ ስለመፈፀም**

በኮሚሽኑ የተቀጠረ ማንኛውም ሠራተኛ ለፌደራሉ ሕገ-መንግስት እና ለከተማው ቻርተር ታማኝ በመሆን የተጣለበትን ሕዝባዊ አደራና ሙያዊ ኃላፊነት ለመወጣት ቃለ-መሃላ ይፈጽማል፡፡ የቃለ-መሃላው ዝርዝር ይዘት በሠራተኞች አስተዳደር ደንብ ይወሰናል፡፡

D. When he reaches the age of retirement.

3. The provisions under letter (A) and (B) of Sub-Article (2) of this Article shall be applied when it is examined by the council and approved by the majority vote of the thereof.

**12. About Recruitment Condition of Employees of the Commission**

The recruitment, administration, and dismissal conditions of the employees of the commission shall be carried out in accordance with a regulation to be issued by the council based on the provisions that are specified under this proclamation and the principles and laws of the civil servants of the city government.

**13. Taking an Oath**

Any individual that is hired by the commission shall take an oath that states his allegiance to the constitution of the federal government and the charter of the city and to fulfill the public trust and professional responsibilities bestowed on him. The details of the oath shall be specified by the employees' administration Regulation.

**፲፬. የኮሚሽኑ ሠራተኞች መብት**

፩. ማንኛውም የኮሚሽኑ የስራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች ደመወዝና ጥቅማጥቅም ከሥራቸው ልዩ ባህሪ ጋር በተያያዘ ምክር ቤቱ በሚያጸድቀው የደመወዝ ስኬል እና ጥቅማጥቅም ውሳኔ መሠረት ተግባራዊ ይሆናል፣ ዝርዝር አፈጻጸሙ በደንብ ይወሰናል፤

፪. የማንኛውም ሠራተኛ ደመወዝ፡-

ሀ) በሠራተኛው ስምምነት፣

ለ) በፍርድ ቤት ትዕዛዝ፣

ሐ) በሕግ በተደነገገው መሠረት፣

ካልሆነ በስተቀር ሊያዝ ወይም ሊቆረጥ አይችልም፤

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተራ ፊደል (ለ) ወይም (ሐ) መሠረት ከሠራተኛ ደመወዝ በየወሩ የሚቆረጠው ከደመወዙ አንድ ሶስተኛ መብለጥ የለበትም፤

፬. ማንኛውም የኮሚሽኑ ቋሚ ሠራተኛ በጡረታ ሕግ መሠረት የጡረታ መብት ይኖረዋል፤

፭. የኮሚሽኑ ሠራተኛ፡-

ሀ) ሥራውን በተገቢው መንገድ በመወጣት ላይ እያለ ለሚደርስበት ተጠያቂነት በመሥሪያ ቤቱ ወጪ ድጋፍና የጥብቅና አገልግሎት ያገኛል፡፡ ዝርዝር አፈፃፀሙ በደንብ ይወሰናል፣

**14. The Rights of the Employees of the Commission**

1. The salary and benefits of any official or employee of the commission shall be applied in accordance with the salary scale and benefits to be issued by the council I light of the special nature of their work; the details of its implementation shall be specified through a Regulation;
2. The salary of any employee may not be withheld or deducted except:
   A. With the consent of the employee;
   B. By a court order;
   C. As specified by the law;
3. The monthly deductible amount from the salary of an employee in accordance with letter (B) and (C) of Sub-Article (2) of this Article should not exceed one third of the salary of the employee;
4. Any permanent employee of the commission shall be entitled to the right of pension according to the pension law;
5. Any employee of the commission shall:
   A. Get support and legal service at the expense of the commission for any accountability incurred on him while properly carrying out his duties; the details of the implementation of the thereof shall be specified through a Regulation;

ለ) በማንኛውም አጋጣሚ የበላይ ኃላፊዎችን በአግባቡ የመጠየቅ፤ ስህተት ሲያይ የመጠቆም፤ ችግሮችን በውይይት የመፍታት እንዲሁም የሥልጣን ተዋረድን ጠብቆ አቤቱታ ማቅረብ ይችላል፣

ሐ) የሠራተኞች ቅሬታንና የዲስፕሊን ጉዳዮችን በተመለከተ በኮሚሽኑ ውሳኔ ቅር የተሰኘ ወይም ያልተስማማ ሠራተኛ ቅሬታውን አግባብ ላለው አካል የማቅረብ መብት ይኖረዋል፡፡ ዝርዝር አፈጻጸሙ በደንብ ይወሰናል፣

መ) ከሥራው ጋር በተያያዘ ሁኔታ በሚደርስበት ጉዳት ዘላቂ ወይም ሙሉ ወይም ከፊል የመሥራት ችሎታውን ያጣ የኮሚሽኑ ሠራተኛ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት የጉዳት ካሳ ይከፈለዋል፤ በጡረታ ሕግ መሠረት የተሰጠው መብት ይከበርለታል፡፡ ዝርዝር አፈጻጸሙ በደንብ ይወሰናል፣

ሠ) መሥሪያ ቤቱን በማሳወቅ በትርፍ ጊዜው ከሥራው ጋር የጥቅም ግጭት የማይፈጥር ሥራ ለመሥራት ይችላል፡፡ ዝርዝሩ ኮሚሽኑ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይወሰናል፡፡

B. Have the right to properly request his superiorly in any circumstances, report any mistakes, resolve problems through dialogue, and lodge complaints following the proper chain of command;

C. Have the right to appeal to the relevant organ if any employee is not satisfied or does not agree with the decision of the commission regarding complaints and disciplinary issues of employees; the details of the implementation of the thereof shall be specified through a Regulation;

D. Get injury compensation, as per the relevant law, if any employee of the commission losses his ability to work permanently, or completely, or partially due to work related injuries; be entitled to his rights that are provided under the pension law; the details of the implementation of the thereof shall be specified through a Regulation;

E. Can engage in any job, through informing the commission, that will not create an conflict of interest with his duties during his leisure time; the details shall be specified through a directive to be issued by the commission.

**፲፭. ሠራተኛን ከሥራ አግዶ ስለማቆየት**

1. የኮሚሽኑ ሠራተኛ ከሥራ ታግዶ መቆየት ለሥራው ጠቃሚ ሆኖ ከተገኘ ሠራተኛውን ከአንድ ወር ለማይበልጥ ጊዜ ከሥራና ከደመወዝ አግዶ ለማቆየት ይቻላል፤
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም የኮሚሽኑ ሠራተኛ በወንጀል ወይም በከባድ የዲስፕሊን ጥፋት በሕግ የተከሰሰ እንደሆነና ተመስክሮበት ጥፋቱ ከሥራው የሚያሰናብተው መሆኑ ሲገመት ለተጨማሪ አንድ ወር ከሥራ ታግዶ ሊቆይ ይችላል፡፡ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፡፡

**፲፮. ስለ ይርጋ ጊዜ**

፩. ቀላል የዲስፕሊን ቅጣት የሚያስከትል ጥፋት የፈፀመ የኮሚሽኑ ሠራተኛ የምርመራውን ጊዚ ሣይጨምር የፈፀመው ጥፋት ከታወቀበት ቀን ጀምሮ እስከ ስድስት ወር እርምጃ ካልተወሰደበት በዲስፕሊን ተጠያቂ አይሆንም፡፡

፪. ከባድ የዲስፕሊን ቅጣት የሚያስከትል ጥፋት የፈፀመ የኮሚሽኑ ሠራተኛ የፈፀመው ጥፋት ከታወቀበት ቀን ጀምሮ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ በጥፋቱ ካልተከሰሰ በዲስፕሊን ተጠያቂ አይሆንም፤

**15. Suspension of an Employee from Work**

1. An employee of the commission may be suspended from his work and salary for a period of not more than one month if his suspension has been found beneficial for the work;
2. Notwithstanding the provision of Sub-Article (1) of this Article, an employee of the commission may be suspended from his work for an additional one month if he is charged with a criminal or grave disciplinary offence and such was testified against him and presumed to lead him to dismissal from work.

**16. About Period of Limitation**

1. An employee of the commission who has committed an offense that entails simple disciplinary measures shall not be liable to disciplinary actions unless a measure is taken within six months from the time the alleged offense is known, excluding the period of investigation;
2. An employee of the commission who has committed an offense that entails grave disciplinary measures shall not be liable to disciplinary actions unless a disciplinary charge is brought against him within one year from the time the alleged offense is known;

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ወይም (፪) በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ መወሰድ የሚገባውን የዲሲፕሊን እርምጃ ሳይወስድ የቀረው ኃላፊ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

**፲፯. በጀት**

ኮሚሽኑ የሚያስፈልገውን በጀት በማዘጋጀት ለምክር ቤት ያቀርባል፡፡ ሲፀድቅ በሥራ ላይ ያውላል፡፡

**፲፰. የሂሣብ መዛግብት**

፩. ኮሚሽኑ የተሟሉ እና ትክክለኛ የሂሣብ መዛግብት ይይዛል፤

፪. የኮሚሽኑ የሂሣብ መዛግብት እና ገንዘብ ነክ ሠነዶች በከተማ አስተዳደር ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ይመረመራል፡፡

**ክፍል ሦስት**

**የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎችን ስለማደራጀት፣ ኮሚሽኑ ከፌደራልና ከክልል የሥነ-ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽኖች ጋር ስለሚኖረው ግንኙነት**

**፲፱. የሥነ-ምግባር መከታተያ የስራ ክፍል ስለማደራጀት**

፩. ኮሚሽኑ በየደረጃው በሚገኙ የአስተዳደሩ መሥሪያ ቤቶች ፣ በአስተዳደሩ የልማት ድርጅቶች እና በህዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ የሥነ-ምግባር ተግባራትን እና የሙስና መከላከል ሥራን የሚያስተባብር እና የሚፈጽም የሥነ-ምግባር መከታተያ የስራ ክፍል ያደራጃል፣

3. An official who fails to take measures within the stated period under Sub-Article (1) or Sub-Article (2) of this Article shall be held accountable.

**17. Budget**

The commission shall prepare its needed budget and submit it to the council. It shall implement the thereof upon approval.

**18. Books of Accounts**

1. The commission shall keep complete and accurate books of accounts.
2. The books of accounts and financial related documents of the commission shall be audited by the office of the Auditor General of the city government.

**PART THREE**

**ESTABLISHMENT OF ETHICS LIAISON DEPARTMENTS, AND RELATIONSHIP OF THE COMMISSION WITH FEDERAL AND REGIONAL ETHICS AND ANTI-CORRUPTION COMMISSIONS**

**19. Establishment of Ethics Liaison Departments**

1. The commission shall establish ethics liaison departments in public offices and public enterprises of the city government at every level which coordinate and carry out ethical issues and corruption prevention activities;

፪. የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል ተጠሪነቱ ለኮሚሽኑ ይሆናል፤

፫. በአስተዳደሩ መሥሪያ ቤት፣ በአስተዳደሩ የልማት ድርጅት እና በህዝባዊ ድጅት ውስጥ የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል ኃላፊ ወይም ሠራተኛ የመመደብ፣ የመቅጠር፣ የማዛወር እና የማሰናበት ተግባር የኮሚሽኑ ይሆናል፤ የሚደራጁት የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎች ስራ ደረጃ በአስተዳደሩ መሥሪያ ቤቶች ወይም በአስተዳደሩ የልማት ድርጅቱ በሚገኙ ዓላማ ፈጻሚ የሥራ ደረጃ ጋር ትይዩ ይሆናል፤

፬. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት በአስተዳደሩ መሥሪያ ቤት፣ በአስተዳደሩ የልማት ድርጅት እና በህዝባዊ ድጅቶች ውስጥ የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል ኃላፊ ወይም ሠራተኛ የመመደብ፣ የመቅጠር፣ የማዛወር እና የማሰናበት ተግባር ሲከናወን በቅድሚያ የየተቋማቱ ማኔጅመንት እንዲመክርበት ከተደረገ በኋላ ይሆናል፤ ዝርዝር አፈጻጸሙ በደንብ ይወሰናል፡፡

2. The ethics liaison department shall be accountable to the commission;
3. It shall be the responsibility of the commission to assign, hire, transfer, and dismiss the head or employee of an ethics liaison department in the public offices or public enterprise of the city government; the career level of the ethics liaison departments to be established in the public offices or public enterprises of the city government shall be parallel with the line personnel of the thereof;
4. The assignment, employment, transfer and dismissal related activities of a head or employee of an ethics liaison department in a public office or public enterprise of the city government according to Sub-Article (3) of this Article shall be carried out after the consultation of the management of the respective institutions on the thereof; the details of it shall be specified through a Regulation.

፳. **ኮሚሽኑ ከፌደራል ፣ ከክልል እና ከድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽኖች ጋር ስነሚኖረው የሥራ ግንኙነት**

፩. የፌደራል የሥነ-ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን የቴክኒክ ድጋፍ እንዲያደርግለት ይጠይቃል፣

፪. ከፌደራል የሥነ-ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ጋር እቅዶች ፣ ሪፖርቶች እና ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎች የሚላክበትን የግንኙነት ስርዓት ይፈጥራል፣

፫. ከፌደራል፣ ከክልል እና ከድሬደዋ አስተዳደር መንግስታዊ ተቋማት ጋር ሙስናን ለመከላከል የሚያገለግሉ መረጃዎችን መለዋወጥ የሚቻልበትን ሁኔታ የስራ ግንኙነት ይፈጥራል፡፡

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

፳፩. **የመተባበር ግዴታ**

ማንኛውም ሰው ኮሚሽኑ በዚህ አዋጅ መሠረት የተሰጠውን ሥልጣንና ተግባር ለመወጣት በሚያደርገው እንቅስቃሴ የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

20. **The Commission's Working Relations with the Federal, Regional and Dire Dawa City Administration's Ethics and Anti-Corruption Commissions**

1. Requires the provision of technical support from the federal ethics and anti-corruption commission;
2. Establish a communication system with that of the federal ethics and anti-corruption commission for exchanging plans, reports, and other necessary information;
3. Establish a working relationship with the federal, regional, and Dire Dawa city Administration governmental institutions to exchange information that helps to prevent corruption.

## PART FOUR

## MISCELLANEOUS PROVISIONS

21. **Duty to Cooperate**

Any person shall have the duty to cooperate in any efforts of the commission in implementing its powers and duties as per this Proclamation.

**፳፪. <u>ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>**

፩. ምክር ቤቱ ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም ደንብ ያወጣል፤

፪. ኮሚሽኑ ይህንን አዋጅና በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወጣውን ደንብ ለማስፈጸም መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

**፳፫. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>**

ይህ አዋጅ በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት በአስተዳደሩ መሥሪያ ቤቶች እና የልማት ድርጅቶች ውስጥ በሥነ- ምግባር መከታተያ ክፍሎች ሲተገበሩ የነበሩ ሥራዎች ከፌደራል የሥነ-ምግባርና ጸረ ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፴፮/፪ሺ፲፫ ጋር እስካልተቃረኑ ድረስ ኮሚሽኑ እስከሚደራጅ ድረስ ሥራቸውን ይቀጥላሉ፡፡

**፳፬. <u>ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች</u>**

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረኑ የአስተዳደሩ ሕጎች በዚህ አዋጅ ውስጥ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፡፡

**፳፭. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ ከ ሐምሌ ፲ ቀን ፪ሺ፲፬ ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሐምሌ ፲ ቀን ፪ሺ፲፬ ዓ.ም.**

**አዳነች አቤቤ**

**የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ**

**22. <u>Power to Issue Regulations and Directives</u>**

1. The council may issue Regulations for the implementation of this Proclamation;
2. The commission may issue directives for the implementation of this Proclamation and Regulations to be issued in accordance with the thereof.

**23. <u>Transitional Provisions</u>**

Activities that are underway in the ethics liaison departments of the public offices and public enterprises of the city government prior to the implementation of this Proclamation shall continue their work until the establishment of the commission unless they contravenes the federal ethics and anti-corruption commission establishment Proclamation number 1236/2021.

**24. <u>Inapplicable Laws</u>**

Any laws of the city government which are inconsistent with this Proclamation shall have no effect on matters that are covered under this Proclamation.

**25. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall enter into force as of this 17th July, 2022

**Done at Addis Ababa, this 17th July, 2022**

**AdanechAbiebie**

**Mayor of Addis Ababa City**